# <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን</u>

# <u>ምእመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር</u>

<u>WORLD ASSOCIATION OF PARISHIONERS OF E.O.T. CHURCH</u>

<u>4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044</u> www.eotcipc.org

miimenan@yahoo.com (214)703 9022


በሰመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር

## <u>ሁለተኛ ጉባኤ ውሳኔ</u>

"ነገር ግን ወንድሞቼ ሆይ አንድ ንግግር አንድትናገሩ በአንድ ልቦና በአንድ አሳብም የተባባራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ።"

1ኛ ቆሮንቶስ ም. ቁጥር 10

1. <u>*መግቢያ*</u>

1.1 የጉባኤው መሠረታዊ ዓላማ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ከውስጥና ከውጭ የተከሰቱባትን ከባድ ችግሮች ለመመርምርና ተገቢ የሆኑ መፍትሔዎች ለመጠቆም እንዲሁም ምዕመናን ከመንፈሳዊ አባቶች ጋር በመተባበር ተጨባጭ እርምጃ በመውሰድ በቤተ ክርስቲያናችን ፍቅር፣ ሰላም፣ አንድነት፣ እድገትና መስፋፋት የሚያስገኙ ሀሳቦችን በተቀናጀና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ መሆኑን በማጤን፣

1.2 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር 2ኛ ጉባኤ መስከረም 19 እና 20 ቀኖች 2004 ዓ/ም (September 30 and October 1/2011) ዋሽንግተን ዲሲ በምትገኘው የርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተከናውኖ፣

1.3 የጉባኤው ተሳታፊዎች ምሑራን፤ ካሕናትና ምእመናን ያቀረቡትን ጥናታዊ ገለጻዎች፤ ውይይቶችና ጽሑፎች መሠረት በማድረግ፤

## 2. ግንዛቤ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ፍሬ ነገሮች በመገንዘብ፡

2.1. የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዓለም አቀፍ ጉባኤ ከኢትዮጵያ፣ ከአውሮፓ እና ከሰሜን አሜሪካ በተሰበሰቡ አንዳንድ ካሕናትና ምእመናን፣ ከልዩ ልዩ ሀገሮች በተገኘ ድጋፍ ከሕዳር 14 እስከ 16 ቀን 1999 ዓ/ም ዳላስ ከተማ በሚገኘው ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል መከናወኑን በማስታወስ፣

2.2. በመጀመሪያው ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የተቋቋመው ግብረ ኃይል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር የተሰኘው ድርጅት በቴክሳስ ሕጋዊ ሕልውና እንዲገኝ በማድረጉ፣

2.3. ማሕበሩ ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆንም፣ ካከናወናቸው ተግባሮች ጥቂቶቹ፣ በቤተ ክርስቲያናችን አባቶች መካከል የተከሰተው አሳዛኝ መከፋፈልና መወጋገዝ እንዲወገድ፣ ኢየሩሳሌም የሚገኘው ታሪካዊ ገዳማችን እንዲጠገን የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ፈቃድ እንዲገኝ፣ የአብነት ትምሕርት ቤቶች ድጋፍ እንዲያገኙ በማበረታታት፣ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ የበላይነት እንዲረጋገጥ፣ እንዲሁም አሠራሯ፣ ትምሕርቷና ስብከቷ በተቀናጀና በቀለጠፈ ስልትና ፕሮግራም እንዲከናወን ጠቃሚ ሐሳቦችን በማቅረብ ጥረት ያደረገ መሆኑን በማሰብ፣

2.4. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀጥተኛና ጥንታዊት በመሆኗና ጽላተ ሙሴን ከእግዚአብሔር ለዓለም ሕዝቦች በአደራ ተቀብላ አቆይታ በአሁኑ ጊዜ የታቦተ ሕግጋቱን ቡራኬና ወንጌሉን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እንዲዳረስ በአሜሪካ፣ በአፍሪካ፣ በቅርብ ምሥራቅ፣ በአውስትራሊያ ወዘተ የተጀመረውን ጉዞ አበረታችነት በመመልከት፣

2.5 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጀርባ አጥንት ሆነው ለዘመናት ያገለገሏትና በማገልገል ላይ ያሉት ገዳማትና አድባራት እንዲሁም የአብነት ትምሕርት ቤቶች ከፍተኛ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በመገንዘብ፣

2.6 በቤተ ክርስቲያናችን አባቶች መካከል በሥልጣንና ጥቅም ምክንያት የተከሰተው መከፋፈል በምእመናን ላይ ያስከተለውን ማናቆርና የሕብረት ማጣት፣ ይህም መሠረታዊ ችግር ያስከተለውን ከባድ ጠንቅ በማጤን፣

2.7 በሀገራችንና በቤተ ክርስቲያናችን ላይ በተጋረጡት የውስጥና የወጭ ችግሮች ምክንያት አጽራረ ቤተ ክርስቲያን፣ ለምሳሌ አክራሪ እስላሞች የሰነዘሩትን ጥቃት በጥንቃቄ በመመልከት፣

2.8 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በረጅም ጊዜ ታሪኳ ከልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች ጋር በመከባበርና በመግባባት ሐዋርያዊ ተግባሯን ስታኪያሂድ መኖሯን ለወደፊትም በዚሁ በሰላም መንገድ ለመቀጠል መርሆዋ ያልተቀየረ መሆኑን በመገንዘብ፣

2.9 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የስብከተ ወንጌል ለጠቅላላው የዓለም ሕዝብ እንዲዳረስ፣ በልዩ ልዩ የዓለም ቋንቋዎች፣ ለምሳሌ በእንግሊዝኛ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን በመገንዘብ፣

2.10 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅድስት ከተማ በኢየሩሳሌም የሚገኘው "ዴር ሡልጣን" የተሰኘው ታሪካዊ ገዳሟ ጥንታዊ ይዞታዋና የሕንጻዎቿም ጥገና ማጣት ለጤንነትና ለሕይወትም አስጊ ደረጃ የደረሰ ከመሆኑም በላይ የተከሰተው መጥፎ ሽታ ገዳሙን አሳፋሪ ሁኔታ ላይ የጣለው መሆኑን በማጤን፣

2.11 በሚሊዮን ለሚቆጠሩት አንዲሁም ብዛታቸው በኃይል እየጨመረ ለሚሄደው በውጭ ሀገሮች ለሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የሚያስፈልገውን ያህል ብቃት ያላቸው ደብሮችና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም የስብከተ ወንጌል አገልግሎት አለመኖሩን በማሰብ፣

2.12 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎቷን በተሟላ ሁኔታ አንድታከናወን በሁሉም ረገድ ራሷን እንደትችልና በሀገራችንም ተንሰራፍቶ ለሚገኘው የድህነት ስቃይ ብቁ የሆነ አስተዋጽኦ እንድታደርግ ማስፈለጉን በማጤን፣

2.13 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር 2ኛ ጉባኤ ከላይ የተዘረዘሩትን ግንዛቤዎች በጥሞና ተመልክቶ ከዚህ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አሳልፏል።

3. <u>ውሳኔዎች</u>

3.1 ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት በመጀመሪያ ጉባዔ ያስተላለፈውን ውሳኔ አጥንቶ የምዕመናን ጉባዔ የቤተ ክርስቲያናችን አንድነት ጉዳይ ለድርድር የማይቀርብ፣ እስኪፈጸም የሚከታተለው መሆኑን በዚህም አጋጣሚ እስካሁን በመደረግ ላይ ያሉትን ጥረቶች አመስግኖ፣ ለወደፊቱም ቢሆን ለሰላምና ለአንድነት የሚደረገውን ጥረት ሁሉ እንደሚደግፍ አረጋግጧል። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም የራሱን ቡድን አቋቁሞ መከታተል እንደሚገባ አስገንዝቧል።

3.2 የአብነት ትምህርት ቤቶችን በሚመለከት እስካሁን በንቡረ ዕድ ገብረ ሕይወት የተቋቋመው ድርጅት በማሕበረ ቅዱሳንና በሌሎች ድርጅቶች የሚደረጉትን ጥረቶች አመስግኖ የችግሩን መባባስና መስፋፋት ተንዝቦ ችግሩን ለመቋቋም የሚሻለውን ዘዴ ባንድ ወጥ ጠቅላላ አመራር መካሄዱን ተቀብሎና አምኖ ይህን የሚወስን አመራር ለማመቻቸት አንድ ግብረ ሀይል ለማቋቋም ተስማምቷል።

3.3 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያንን የቅዳሴ ሥርዓት በእንግሊዝኛ በዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ስለ ማቅረብ በርዕሰ ደብር አብርሃም መሪነት በዲያቆን ቤዛ ቢልልኝ ረዳትነት ተዘጋጅቶ የቀረበለትን በምስጋና አዳምጦ ስለ ጥረቱ አድንቆ ስራው የሚያጓጓ በመሆኑ በተቻለ ፍጥነት ተጠቃሎ እንዲቀርብ አዘጋጆችን ተማጥኗል። በሚያስፈልግ እርዳታ ሁሉ የምእምናን ማሕበር እንዲተባበር ጠይቋል።

3.4 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያን ታሪክ ምዕመናን ከአባቶች ካህናትና መነኮሳት ጋር በቅርብ በመተባበር ለቤተ ክርስቲያናችን ደህንነትና መስፋፋት ያበረከቱት አስተዋጽኦ ግዙፍ ነው። ብርታታቸውና አይበገሬነታቸውም የሚደነቅ ነው። ይህ ሲወርድ ሲዋረድ ሳይበርድና ሳይደክም በመካሄዱ ይኸው በዛሬውም ጊዜ ቤተ ክርስቲያናቸው እየገጠሟት ያሉትን ችግሮች በጸሎታቸው በመማጸን፣ በጉልበታቸውም በገንዘባቸውም በጠቅላላው ባላቸው አቅም ሁሉ እያደረጉ ያሉትን አስተዋጽኦ ጉባኤው በአጽንኦት ተገንዝቧል። ወደፊትም ቢሆን ባገራችንም ውስጥ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተፈነጠቀውና እየተካሄዱ ያለት እንቅስቃሴዎች በቤተ ክርስቲያናችን ላይ እያደረሱ ያሉት ተጽእኖ አስጊ ደረጃ በመድረሱ፣ ምዕመናን ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ ነቅተው መጠባበቅ እንዳለባቸው ጉባኤው ያሳስባል። በተጨማሪም የምእመናን ጉባኤ የጊዜውን ሁኔታ በማገናዘብና

መዋቅሩን በማጠናከር  ጉልበቱን ገንዘቡንና የዲፕሎማሲ ጥበቡንና ኃይሉን በማስተባበር አስተዋጽኦ እንዲቀጥል አጥብቆ ያሳስባል።

3.5 ስለ ዴር ሡልጣን ገዳም በተደረገው ውይይት ገዳሙና በገዳሙ ውስጥ የሚኖሩት መነኮሳት የሚኖሩባቸው ክፍሎችና ቤቶች ባለመታደሳቸው ለጤና ጠንቅ ደረጃ እንደደረሱ በታላቅ ኀዘን ተገንዝቧል። ሁለተኛ ይህን ጉዳይ በቅርበት ሆኖ የሚከታተለው በእሥራኤል ውስጥ የተቋቋመው ማህበረሰብ ይህን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተል ልዩ ኮሚቴ መዋቀር ላይ መሆኑን በደስታ ካዳመጠ በኋላ፡-

3.5.1 በእሥራኤል የተቋቋመው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ተወካዮች በመካከላችን በመገኘታቸው የተሰማንን ደስታ ለአባሎቻቸው ከአክብሮት ምሥጋና ጋር እንዲያቀርቡልን፣

3.5.2 ይህ ጉባዔ ባለው አቅም ሁሉ ሕዝቡን በማስተባባር በግንዛቤና በዲፕሎማሲም ረገድ ድጋፍ ለመስጠት ስምምነት መድረሱን፣

3.5.3 በወንድማችን በዶክተር ካሣ ከበደ ስለ ዴር ሡልጣን የተዘጋጀው ጥናት ተጠናክሮ ለግንዛቤ እንዲያገለግል እንዲታተም፣

3.5.4 የዴር ሡልጣን አንገብጋቢው ጉዳይ የኢትዮጵያና የዓለም ሕዝብ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ልዩ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች እንዲሳተፉ እንዲተባበሩ አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማኅበሩ እንዲያካሂድ ተወስኗል።

3.6 ከኢትዮጵያ ውጭ የሚወለዱና በሕጻንነት መጥተው ኢትዮጵያዊ ባልሆኑ ባህሎች በማደግ የባህል ግጭቶች መፈንጠቃቸው አልቀረም።  እንደዚህ ያለውን ችግር ለመቋቋም ወይም ለመቀነስ ያገራቸውን ቋንቋ በማስተማር በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ቋንቋዎች በማስተማር ለመግባቢያ የሚጠቅሙ ለእድሜ ደረጃ የሚያገለግሉ መማሪያ መጻሕፍት እንዲያዘጋጁ በማበረታታት ያስተማማሩን ውጤትም በምርምርና በመገምገም ልንቋቋመው አንድንችል፣ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ቋንቋንዎች ለምሳሌ በእንግሊዝኛ  በመጠቀም የቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ትምህርት በዓለም ደረጃ እንዲስፋፉ ጥረት እንዲደረግ ማስፈለጉ ታምኖበታል።

3.7 በተጨማሪም ማኅበሩ  የሚመራበትን ረቂቅ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ፣ የማኅበሩን አወቃቀርና ገንዘብም እንዴት ማመንጨት እንደሚቻል የተጠኑ ጥናቶች ቀርበውልን በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ሀሳቦችን በጽሁፍ ለማኅበሩ እንዲቀርብ ተጠይቋል። ከምዕመናኑ  የሚቀርቡት ልዩ ልዩ ሀሳቦች ተሰባስበው ወደ ተቋቋመው የማሕበሩ አመራር ተመርቶ፤ አጣርቶ በተግባር ላይ

እንዲያውልና ወደፊት ለሚያስፈልገውም መሻሻል ቢያንስ ዘዴውን ቀይሶ ለሚቀጥለው ጉባኤ በማቅረብ እንዲያጸድቅ ኃላፊነት ተሰጥቷል።

በመጨረሻም፤ ጉባኤው በተስካ ሁኔታ እንዲከናወን ከፍተኛ አሰተዎጽኦ ላደረጉት በተለይ ለርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድሰት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፤ ካሕናትና ምእመናን፣ እንዲሁም በገንዘብና በልዩ ልዩ የአገልግሎት ድጋፍ ላበረከቱትና እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ጥናታዊ ጽሑፎች ላቀረቡት ምሑራንና በውይይቶቹ ለተሳተፉት ሁሉ ጉባኤው ጥልቅ ምሥጋውን እቅርቦ ውሳኔዎቹም ተግባራዊ እንዲሆኑ ሕብረታችን እንዲቀጥል ቸሩ እግዚአብሔር እንዲረዳ በመጸለይ ጉባኤው ተፈጽሟል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር። አሜን